# <u>እውነት ተደብቆ አይቀርም!!</u>

ከማርቆስ ዓለሙ ከሚድዌስት አሜሪካ

ጥር 27 ቀን 2012ዓም

## <u>መግቢያ</u>

እውነት(Truth) የሚለው ቃል ትልቅ ክፍልስፍና ጋር የተያየዝ ሀሰትን ለይቶ ለማወቅ የሚረዳ ነው። ከእምነትም ጋር የሚያየዝ ነው። እምነት ቃል ኪዳን ነውና መጠበቅ ያለበት ነው። በሁሉም የሰው ልጅ የተግባር እንቅስቃሴ ውስጥ ትልቅ ቦታ አለው።ለምሳሌ በማስተማር ዘርፍ መምህራን የሚያስተምሩትን ትምህርት እውነታ(Facutal Accuracy) በትክክል ለተማሪዎች ካላስተላለፉ የሀሰት ትምህርት ሰጥተው ተማሪውን ቀጥሎም ከትምህርቱ ተጠቃሚ የሚሆናውን አገርና ህዝብ ይጎዳሉ። በአጠቃላይ በሁሉም የሳይንስ ዘርፎች ማለትም በተፈጥሮና በማህበራዊ ሳይንስ የሚሰጠው መረጃ እውነት ነው። አለበለዚያ በአገርና በሕዝብ ላይ የሚያደርሰው አደጋ ከበድ ነው።በዓለም ላይ ሀቅ ተዘብቶ የሰው ልጅ ችግር ላይ መውደቅ ከጀመረበት ቆይቷል።የአፍሪካን የምዕራባውያን ቅርምትን ማስታወስ ተገቢ ነው። የቅኝ አገዛዝ ስርዓት ተወግዶ "ዘመናዊ የአስተዳደር ስርዓት" በአለም አቀፍ ደረጃ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በኢትዮጵያ የመንግስት ስልጣን የያዙ መሪዎችና ተከታዮቻቸው በህዝብ ስም እየመሉና ለህዝብ የሚሰሩ መስለው እውነትን በመደበቅ ህዝብን በፖለቲካው ሲጨቁኑ፣ ኢኮኖሚውን ሲበዘብዙና የማህበራዊ ቀውስ ሲያደርሱ ቆይተዋል። ለአገርና ለህዝብ በቆሙ ድርጅቶች፣ ተቋማት፣ ማህበራትና ግለሰቦች ላይ ጥቃት በማድረስ የስልጣን ዘመናቸውን ሲያረዝሙ ኖረዋል። የዚህ አጭር ጹሁፍ መልዕክት በኢትዮጵያ ልጆች ተመስርቶ፣ ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ አገራዊና ሕዝባዊ ሏዓላዊነት፣ የስልጣን ምንጭነትና ባላቤትነት፣ ለሕግ የበላይነት ከተመሰረተበት ከ1964 ዓም ጀምሮ በመተጋል ላይ በሚገኘው ኢሕአፓ ላይ ውስጥ ለውስጥ ተደራጅተው አንጃ ሆነው የወጡ ግለሰቦች፣ የድርጅቱ አባል ነበርን የሚሉ አስመሳዮች ሕዝብን ለማወናበድ የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ ማጋለጥና ለህዝብ እውነታውን ማሳወቅ ይሆናል።

## <u>የአሁኑ የኢሕአፓን ስም ሰርቆ አዲስ አበባ የገባው አንጃ እንቅስቃሴ</u>

የኢሕአፓ አባላት የነበሩና ያሉ ብርቅዬ የኢትዮጵያ ልጆች ትናንትናም ሆነ ዛሬ ያነሱትን ሕዝባዊና አገራዊ ጥያቄዎችን ማለትም የመሬት ላራሹ፣ ያኔ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት፣ ዛሬ ጊዜያዊ ሕዝባዊ የሽግግር መንግስት፣ ዲሞክራሲ ያለገደብ፣ የሕግ በላይነት ይከበር፣ የሴቶች የእኩልነት መብት ይከበር፣ የሙያና የሲቪክ ማህበራት የመደራጀት መብታቸው ይከበር፣ የእምነት እኩልነት ይከበር፣ ዘረኝነትና ጠበብነት ይወገድ፣ የኢትዮጵያና የህዝቧ አንድነትና ሉዓላዊነት ይከበሩ ባጠቃላይ የኢኮኖሚ ብዝበዛ፣ የፖለቲካ ጭቆናና የማህበራዊ ችግሮች ሁሉ የሚወገድበትን መንገድ እየፈለጉ በሚገኙበት ወቅት ነው የአቢይን እግር ልሶ የኢሕአፓን ስም ሰርቆ ወደ አዲስ አበባ የገባው አንጃ ኢሕአፓ ወያኔን በደብዳቤ ይቅርታ ጠይቆ አገር ቤት ይግባ የሚሉትን እንቅስቃሴ የጀመሩት በከፍተኛ አመራር ኮሚቴ ውስጥ ነበር። ቁጥራቸው ትንሽ ነበር ። አመራር ኮሚቴው በድምጽ ብልጫ ጥያቄያቸውን እዚያው ማስቀረት ሲችል በአባላቱ ጥንካሬ፣ በውይይትና በዲሞክራሲያዊ አስራር እምነት ስለነበረው ወደ አባላት አወረደ። አባላት ውይይት አድርገው ውድቅ አደረጉ። ለአራተኛ ጠቅላላ ጉባኤም ቀርቦ በጉባኤተኞቹ ከፍተኛ ድምጽ ውድቅ ሆነ።ይህ ከፍተኛ አመራር ኮሚቴ ውስጥ መሽጎ የነበረው የጥቂት ሴራኞች ቡድን አራተኛው ጉባኤ በሰየመው አመራር ውስጥ በመግባታቸው የድርጅቱ ስራ እንዳይሰራ ለማድረግ ጥረት በማድረጋቸው 5ና 32 ገጾች ያሉት ወረቀቶች ከአመራር አካላት ስማቸው ሳይጠቀስ ለአባላት እንዲታላለፍ ተደረገ። 5ገጾች የነበሩት ወረቀት በድርጅቱ ከፍተኛ አመራር ኮሚቴ ያሉት አፉዳቢት(Afadavit= A written statement confirmed by oath or affirmation, for use as evidence in court)የቃል ኪዳን ሰነድ ኢሕአፓ ወያኔን ይቅርታ የሚጠይቅ ደብዳቤ ጽፎ አገር ቤት መግባት አለበት የሚሉት ማስቸገራቸውን እንዲሁም ሌሎች ጉዳዮችን የድርጅቱን ምስጥር በሚጠብቅ መልኩ ሲያቀርብ፤ይህ ጽሁፍ በአባላት ዘንድ ድጋፍ ነበረው፣32 ገጽ ወረቀት የድርጅቱን ምስጥር ያልጠበቀና ድርጅቱን ወደፊት ለአደጋ የሚጥል በመሆኑ አባላት ውድቅ በማድረግና ውሳኔ በማስተላለፍ የድርጅቱ ልዩ ጉባኤ በአስቸኳይ እንዲጠራ ተስማሙ። የድርጅቱ አስቸኳይ ልዩ ጉባኤ ጥቅምት 18 ቀን 2000ዓም( October29, 2007) ተደረገ። ከዚህ ጉባኤ ተገኝተው ሀሳባቸውን ሳይሰጡ አቶ መርሻ ዮሴፍ ከሌሊቱ 9 ሰዓት ስብሰባው ከሚካሔድበት ሆቴል ጠፉ፤ ሌሎች በነጋታው ወደ ጉባኤ አደራሽ ገብተው ውይይቱ ሳይጀመር ስብሰባውን ረግጠው ወጡ። የቀሩት አብዛኛዎቹ የድርጅቱ አባላት

ስብሰባቸውን ቀጥለው ውሳኔዎችን በማስተላለፍ ድርጅቱ ስራውን እንዲቀጥል አድርገዋል።ህዝብ እንዲያውቅ የምፈልገው ድርጅቱ ሁሉንም ጉዳይ ደረጃ በደረጃ አባላትን በማሳተፍ ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ለመፍታት ያደረጋቸውን እንቅስቃሴ ነው። በሌላ በኩል የድርጅቱን ደንብ ጥሰው፣ለውይይት በር ዘግተው፣ ለአባላትና የወደቁ ጓዶች አደራ ለሰጡት ቃል ኪዳን ቦታ ሳይሰጡ ለወያኔ ተላላኪና ስልጣን ፈላጊ የሆኑ ጥቂት ግለሰቦች አንዳንድ አባላትንም አሳስተው አንጃ ሆነው ኢሕአፓ( ዲሞክራሲያዊ) በማለት በኢሕአፓ ላይ በድርጅቱ ታሪክ ተለጣፊ ለመጀመሪያ ጊዜ የፈጠሩ መሆናቸውን ነው። ከታች ስሙን የሚጠቅሰው ግለሰብ ከእነሱ ጋር አብሮ ይሰራ የነበረው እንደመሰከረው ብዙም ሳይቆዩ ተበተትነዋል፤ ኢሕአፓ ህዝብን እንዳያወናብዱ ፍርድ ቤት ከሶ የድርጅቱን ስም፣ ሊሳንና ዓርማ እንዳይጠቀሙ በማድረግ ከጥቅም ውጪ አድርጓቸዋል።ኮሎኔል አቢይ የወያኔ ሹም ግን እነዚህን ጥቂቶች የኢሕአፓን ስም ሰርቀው ሕዝብን እንዲያሳስቱ፣ ተላላኪዎቹ እንዲሆኑ ለማድረግ አገር ቤት እንዲገቡ አድርጓል። የኢትዮጵያ ህዝብ እነዚህን የትግል ጸሮችን በማወቅ ከጥቅም ውጪ ማድረግ ያስፈልጋል።ቀደም ብለው የድርጅቱ አባላት የነበሩትም ይህን ጉዳይ በአንክሮ መከታተል ይኖርባቸዋል። የውሸት መጽሀፍት በመጻፍና የተለያዩ ጽሁፎችንና ተረካዎችን በማቅረብ አዲሱ ትውልድ ስለድርጅቱ እውነታውን እንዳያውቅ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት የሚያደርጉት ወያኔዎችና ቅጥረኖቻቸው፣ዘረኞችና ጠበቦች፣ በደርግ ስርዓት ነፍሰገዳዮች የነበሩ፣ አንጃዎች፣ የኢትዮጵያ የውጭ ጠላቶች፣ ድርጅቱን በሚመለከት ምንም ዓይነት ጥናት ሳያካሄዱ በአሉታዊ መልኩ በወሬ በሰሙት ትክክል ባልሆነ መረጃ የሚዘምቱ ግለሰቦችና አንዳንድ የድሮ ስርዓቶች ናፋቂ የሆኑ ሕልመኞች ናቸው።

## *ለድርጅቱ ያሰቡ በመምሰል በህቡዕ የሚሰራውንና እውነተኛ ኢሕአፓን ማጥቃት*

አቶ ነሲቡ የተባለው ግለሰብ "ኢሕአፓ ለምን ተከፈለ? ዛሬስ ምን መደረግ አለበት?" በሚል ርዕስ በኢትዮላይን ድረገጽ ላይ የለጠፈው ጽሑፍ ለኢሕአፓ የሚቆረቆር መስሎ በድርጅቱ ላይ ጥቃት የፈጸመ ነው ። ይህ ግለሰብ በወያኔ ተልኮ በሆላንድ አገር ትምህርቱን የተማረ፣ እዚያ በነበረበት ወቅት በሆላንድ አገር በደንብ የሚታወቀውን ኢሕአፓንና አባላቱን ሊያገኛቸው አልቻልኩም በማለት፣ከወያኔ የተሰጠውን ስምሪት ለመወጣት ሲል ኢሕአፓን በመፈለግ ጭምብል ወደ ሰሜን አሜሪካ በመሄድ ወደ ኢሕአፓ ጽ/ቤት በመቅረብና በአካባቢው ከነበሩ አባላት ጋር ቅርርቦሽ ፈጥሮ ለተወሰነ ጊዜ ቆየ። ወያኔን ኢሕአፓ በደብዳቤ ይቅርታ ጠይቆ አገር ቤት መግባት አለበት፣ የወያኔን ህገ መንግስት በመደገፍ አገር ቤት በሕጋዊነት ይመዝገብ፣ወያኔን ወያኔ አንባል ኢህአዴግ እንበል፣ ድርጅቱ ሊቀመንበር ይኑረው፣ የትግል ስልቱን ወያኔ በሚፈልገው መልክ ይለወጥ በማለት በድርጅቱ ከፍተኛ አመራር የነበሩት ጥቂቶች ባነሱት ጉዳይና በሌሎችም ላይ ውሳኔ ለመስጠት በጥቅምት ወር 2007 እንደ አውሮፓ አቆጣጠር የድርጅቱ አስቸኳይ ልዩ ጉባኤ በሚካሄድበት ስብሰባ ላይ ሊገኝ ሂዶ አለቃው መርሻ ዮሴፍ በውድቅት ሌሊት ከምሽቱ 9 ሰዓት እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ሲጠፋ ከላይ ስሙ የተጠቀሰው ግለሰብ በነጋተው ጧት የድርጅቱን ጉባኤ ረግጦ ወጥቶ በድርጅቱ ላይ አንጃ ከፈጠሩት ውስጥ አንዱ ነው።ይህን የአንጃነቱን ተግባር ለመደበቅ ኢሕአፓ ለሁለት ተከፈለ በማለት ከህቅ የተጣላ መረጃ ለህዝብ ለማስተላለፍ ይጥራል። ከዚያ በፊት ወጣቶችን ለማደራጀት ሲታሰብ የወጣት ክንፉ ከድርጅቱ ስር እንዳይሆን ሀሳብ አቅርቧል። በተለያዩ ጽሑፎች ግን ለድርጅቱ ወጣት ክንፍ ያሰበ በመምሰል ይከትባል። ይህ ግለሰብ ይህን አድርጌአለሁ ፤ የዚህ ደራሲ ነኝ በማለት በጽሑፉ ገጽ 2 አንቀጽ 2 ከጠቀሳቸው ውስጥ፡-

*በያ ትውልድ ተቋም (http://www.yatewlid.com) የቀይ ሽብር ሰማዕታት በሚለው ስር ከተጻፉት ውስጥ **ሸዋ በካምባታና ሀዲያ በ1969/70/71 በደርግ /መኢሶን/ወዝሊግ/ኢጭአት በቀይ ሽብር የተገደሉ** ተብሎ በሰንጠረዥ በቀረበውና እንዲሁም **ሸዋ ከምባታና ሃድያ፡- ሆሳዕና በታህሳስ 16, 17 ቀን 1970ዓም በደርግ ቀይ ሽብር የተገደሉ** በሚል በሌላ ሰንጠረዥ በቀረበው ላይ ያለውን ውሸት ለህዝብ አቅርባለሁ፡-*

- በአውራጃው ውስጥ በህዝብ ልጆች ላይ ግድያ የተፈጸመው ከላይ በተጠቀሰው መሰረት በአውራጃው ስም ከምባታና ሀዲያ እና በአውራጃው ዋና ከተማ ሆሳዕና ተብሎ አልነበረም። አንባቢያን እንዲያውቁት ከምባታና ሀዲያ የአውራጃው ስም ሲሆን ሆሳዕና የአውራጃው ዋና ከተማ ነው።
- ግድያዎቹ የተካሄዱትም በተለያዩ ዓመታት 1969፣ 1970ና 1971 አልነበረም።ከምባታ ሀድያ አውራጃ በቀይ ሽብር የተገደሉትን በሚመለከት በተዘጋጀው ሰንጠረዥ መግለጫ በሚለው ስር እንደተገለጸው 10 ሰዎች ከምባታ ተብሎ ተቀምጧል። ምን ለማለት ነው? ግድያው በዘር ምደባ ነው ለማለት ከሆነ በዚያ መልኩ አልነበረም። ወያኔ ያመጠብንን የዘር ምደባ ተጠቅሞ ለማስቀመጥ ከሆነም የሞተው አንድ ሰው ነው። 9ኙ

ከየት የመጡ ናቸው? ሙያቸውም ትክክል አይደለም ፤ ለምሳሌ ከብዙዎቹ አንዱ ፋንታሁን መዘምር የጤና ጣቢያው ሂሳብ ሹም እንጂ ሐኪም አልነበረም።በ1969ዓም እና 1970ዓም ምንም ዓይነት ግድያ አልነበረም። መረጃዎቹን የወሰደበትን ቦታ ላለመግለጽ የተደረገ ቅጥፋት ነው። አንባቢያን እንዲያውቁት ከምባታ በአውራጃው የሚገኝ የአንድ ብሄረሰብ ስም ሲሆን ሀድያም በአውራጃው የሚገኝ የሌላ የብሄረሰብ ስም ነው።

- በከምባታና ሀዲያ ተገደሉ ተብሎ በሰንጠረዡ ላይ ስማቸው ከተጠቀሱት ውስጥ አደነ መኮንን፣ መንግስቱ ወርቁ፣ ንጉሴ መንግስቱ፣ ተሰፋዬ ዘዉዴ፣ ስንታዬሁ ወንድሙ፣ ሉሌ አባተ፣ መኮንን አማረ ተብሎ የተለጸው ውሸት ነው። እነዚህ ወገኖች በአካባቢው አልተገደሉም፤ በእስር ቤቶቹም አልነበሩም።
- እንዲሁም በሆሳዕና ተገደሉ ተብሎ በሌላ ሰንጠረዥ ውስጥ ስማቸው ከተጠቀሱት ውስጥ ያሬድ ታደሰ ከመግለጫ ላይ አዋሽ ቆቃ ተብሎ የተገለጸው ውሸት ነው። ይህ ግለሰብ በአካባቢው አልተገደለም፤ በእስር ቤቶቹም አልነበረም። አዋሽ ቆቃም በአውራጃው ውስጥ የማይገኝ ቦታ ነው። ይህ የሚያሳየው የግለሰቡን አውራጃውን በሚመለከት ያለውን አነሳ እውቀትና ህዝብን በውሸት መረጃ ለማታለል የሚያደርገውን ከፍተኛ ወንጀል ነው።
- በሆሳዕና በታህሳስ 16ና 17 ቀን 1970 ዓም ምንም ዓይነት ግድያ አልነበረም።እስርም አልተደረገም።
- ግለሰቡ ሸዋ በከምባታና ሀዲያ አውራጃ በደርግ/መኢሶን/ወዝሊግ/ኢጭአት በቀይ ሽብር የተገደሉ በማለት ከአስቀመጠው ውስጥ ግድያው በተካሄደበት በ1971ዓም መኢሶንና ኢጭአት አልነበሩም ።መኢሶን ተሙቶ በወቅቱ የአውራጃው የሕዝብ ድርጅት ጊዜያዊ ጽ/ቤትን ተቆጣጥሮ የነበረው ወዝሊግ ነበር።
- ሸዋ በከምባታና ሀድያ አውራጃ ***የተለያዩ ወረዳዎች*** በደርግ/መኢሶን/ ወዝሊግ/ኢጭአት የተገደሉ መግቢያ ገጽ በማለት ርዕስ ሰጥቷል። በአዉራጃው ውስጥ በተለያዩ ወረዳዎች ግድያ አልተካሄደም።

እውነታው በ1971ዓም የኢሰፓ ተለዋጭ አባል የነበረውና በሲዳሞ ክፍለ ሀገር ከሙቶ አለቃ ተስፋዬ ቼንቶ ጋር በማበር የኢሕአፓ አባላትን በቀይ ሽብር ያጠፋው፤ አውሬው፣ ማሃይሙ፣ ዘረኛውና የሴት ቀመኛ የነበረው ሙቶ አለቃ ጴጥሮስ ገብሬ የአውራጃው አስተዳዳሪ ሆኖ ከተመደበ በኋላ ቀይ ሽብር አዋሽን አይሸገርም ያለው ማን ነው በማለት ዝቶ ከሁለት አንጃዎች አንዱ( ደሳለኝ ጀፎ) የእሱ ዘመድ የሆነውን ስልጣን ሰጥቶ መጠቀሚያ በማድረግ በ1969 ዓም በመኢሶን አባላትና በስርዓቱ ፖሊሶች ተደብድበው 6ወር ከ18 ቀናት እስረት በኋላ ተፈትተው በአገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች በስራና በትምህርት ገበታ ላይ ይገኙ የነበሩትንና በአውራጃውም ይኖሩ የነበሩትን በካድሬዎቹና በወታደሮች አስይዞ ወደ ሆሳዕና እንዲመጡ አድርጎ በሆሳዕና ከተማ በሚገኛው ከርቼሌና ያንድ የአውራጃው ፖሊስ አዛዥ ኮሎኔል ቤት የነበሩትን ሁለት ክፍሎች ጸሀይና ብርሃን እንዳይኖር ተደርገው ወደ እስር ቤትነት ለውጠው የላይኛውን ክፍል የማሰቃያ የታችኛውን ክፍል የማጎሪያ አድርገው በመጠቀም በወቅቱ ይደረጉ የነበረውን የግፍና ሰቆቃ ዓይነቶችን በሙሉ ከፈጸሙ በኋላ ጴጥሮስ ገብሬ ከለገሰ አስፋው ጋር በመሆን በሰጠው ትዕዛዝ የመጀመሪያ ዙር ግድያ ሰኔ 25 ቀን 1971ዓም በ15 የኢሕአፓና የሕዝብ ልጆች ላይ አጀራ በሚባል ቦታ በኡሩምታ ተኩስ ተገድለው ባንድ ጉድጓድ እንዲቀበሩ ተደርጓል፡፡። የሁለተኛ ዙር ግድያ በ21 የህዝብ ልጆች ላይ ነሐሴ 21 ቀን 1971ዓም ጨጫ በሚባል ቦታ በኡሩምታ ተኩስ ተገድለው ባንድ ጉድጓድ ውስጥ እንዲቀበሩ ሆኗል።ባጠቃላይ 36 የህዝብ ልጆች በግፍና አረመኔያዊ በሆነ መንገድ የቀይ ሽብር ሰለባ ሆነዋል። የነዚህን ታጋዮች ግድያ በሚመለከት ከግድያው ያመለጡና የተረፉ የድርጅቱ የአሁኑና የቀድሞ አባላት ዝርዝር ሁኔታዎችን በእንግሊኛ አዘጋጅተው ሁለት ጊዜ ለአሲምባ ድረገጽ(www.assimba.org) እንዲለጠፍ ተልኮ ድረገጹም ( Red Terror Victims Memorial Page) በሚለው ሊንክ " ***<u>The red Terror Victims in 1971(1979) at Hossaena in Kembata and Hadiya Awuraja, Southern Shoa, Ethiopia</u>***" እና "Central Ethiopia- Hossaena-Shoa በሚል ርዕሶች ለጥፏል።ክብርና ምስጋና ለድረገጹ ይሁን። ሌሎች ወገኖች ድረገጹን በመጎብኘት ይህን ሀቅ እንዲመለከቱት እጠይቃለሁ።

ያ ትውልድ ተቋም በከምባታና ሀዲያ አውራጃና በሆሳዕና የቀይ ሽብር ሰማዕታት በማለት የዘረዘረውን ስሞች የሰረቀው ከአሲምባ ድረገጽ ነው፣ መረጃዎችን ግን የራሱ ለማስመሰል አሳስቶ ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ ለውጦ ያልሞቱትን ሰዎች ስም ጨምሮ አስቀምጧል።ለምሳሌ Matiwos Tumoro ተብሎ በአሲምባ ድረገጽ ገጽ በእንግሊኛ የተጻፈውን በአንደኛው ሰንጠረዥ ላይ ማቲዎስ ጠምሮ በሌላኛው ሰንጠረዥ ማቲዎስ ቱሞሮ በማለት አስቀምጧል። የአባት ስም ስህተት ነው፣ ትክክለኛው ጡሞሮ ነው።ስሙን ከአሲምባ ድረገጽ ለመውሰዱ ትክክለኛ ማስረጃ ነው። የሰውን ስራ ያለፈቃድ ወስዷል። ይህ ነውር ነው፣ አጭበርባሪነትና ስርቆትም ነው። ተቋሙ በድረገጹ ላይ መረጃዎቹን የወሰደበትን ቦታ ደብቆ ከመረጃዎቹ

ላይ የተለያዩ ስህተቶች ካሉ እርማት እንዲደረግ ማሳሰቢያ ይሰጣል። በቅን ልቦና ቢሆን ኖሮ ጥሩ ነበር። አንጃኘነት ሁልጊዜ ከቅን ልቦናና ከንጹህ ሕሊና የረቀ ስለሆነ ይህ ከእነሱ የሚጠበቅ አይሆንም ።ግለሰቡም የፈጸመው ያው የአንጃ የለመደበት ቅጥፋት ነው። በዚህ አጋጣሚ ሌሎች ወገኖች በሌሎች የአገሪቱ ክፍሎች በያ ትውልድ ተቋም ላይ የቀይ ሽብር ሰማዕታት ስም ዝርዝርና ትርክቱን እንዲመለከቱት እጠይቃለሁ።

የቀይ ሽብር ተሳታፊዎች በሚል ስር ከተዘረዘሩት ውስጥ በከምባታና ሀዲያ አውራጃ ዋና ተዋናይና የግድያ ትዕዛዝ ሰጭ በነበረው መቶ አለቃ ጴጥሮስ ገብሬ ላይ የሞት ፍርድ እንድተበየነበት ይገልጻል፤ ይህን ነፍሰ ገዳይ ወያኔ ለቆት በአዲስ አበባ በነፃ መኖር ከጀመረ ዓመ ታት አልፏል ። ሌሎችም እንዲሁ ተፈተዋል። እና ፍቅረሰላሴ ወግደረስና ፍስሐ ደስታ የሐሰት መጽሐፍ በመጻፍ በኢሕአፓ ላይ እየዘመቱ መሆኑ ከታወቀም ቆይቷል። ለምን ይሁን ማስተካከያ በተቋሙ ድረገጽ ላይ ያልተደረገው? ወያኔን ለመጥቀም ነው? ወያኔ ፍርድ ተሰጥቶ አስረኩ ሲልም ህዝብን ለማታለልና ጊዜያዊ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት ነበር። የወያኔ ዋና ጠላቶች የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ኢሕአፓና አገር ወዳድ ዜጎች ናቸው።ይሕንንም የኢሕአፓ አባላትንና ሌሎች ኢትዮጵያዊ አጀንዳ ይዘው ሲታገሉ የነበሩትን ከግለስብ ጀምሮ ገድሎ፣ አስሮና ደብዛቸውን አጥፎ አስመስክሯል። ለመሆኑ በተቋሙ ድረገጽ ላይ ኢሕአፓ የገደላቸው ተብሎ የተቋሙ ዓርማ የተደረገባቸው ሰዎችን በሚመለከት በኢሕአፓ በኩል ስምምነት አለ ወይ? ወይስ ግለሰቡ ራሱንና ተቋሙን ብቻ እንደ ወሳኝ አካል ቆጥሮታል? በተቋሙ ድረገጽ የተለጠፉት መረጃዎች ምንጮቹ ከየት እንደሆኑ መጠየቁ የማይቀር መሆኑንም መገንዘብ ያስፈልጋል። ተቋሙ መረጃዎችን ያገኘበትን ምንጮች አልጠቀሰምና።

በተቋሙ ድረገጽ ላይ የዴሞክራሲያ ዕትሞችን ዝርዝር አይቼአለሁ። ከቅፅ 43 -45 ድረስ ያሉት ለምን ይሁን ያልታተሙት?

ይህ ግለሰብ "አንድ አገር አንድ ህዝብ ኢትዮጵያ ህዝባዊ ንቅናቄ" የሚል ድርጅት መስርቶ የመደመርን ቃል ተቀብሎ ለአቢይ አገዛዝ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኝ ነው። ለዚህም ማስረጃ መርፌ ቅፅ 1 ቁጥር 4 መጋቢት 2011ዓም "ትግል ወሬ አይደለም" በሚል ርዕስ በሰጠው ቃለ መጠይቅ ንቅናቄው ከነሐሴ 21 ቀን 2011ዓም ጀምሮ መሉ በሙሉ አገር ቤት የምንቀሳቀስ መሆኑን ገልጿል። የራሱን ድርጅት መስርቶ ክምርጫ ቦርድ ኃላፊና ክሹሙ ጋር ተስማምቶ "ለውጡን" ተቀብሎ የሚሰራ መሆኑን የገለጸ ሰው ነው ኢሕአፓ ነበርኩ በማለት በድርጅቱ ላይ እየዘመተ የተላላኪነት ሚናውን በመጫወት ላይ የሚገኘው። የተረኞቹ ሹምና የተከታዮቻቸውን የኢትዮጵያ ህዝብ ጠላትነት ገና ከመነሻው ተገንዝቦ ህዝቡ ለስልጣን ምንጭነትና ባላቤትነት ወሳኝ ለሆነው ለሽግግር መንግስት ምስረታ በማስተማር ላይ የሚገኘውን ኢሕአፓን ለስርዓቱ ታማኝ ከሆነው የኢሕአፓን ስም ሰርቆ በአዲስ አበባ ካለው አንጃ መሪ ጋር የተጣላ መስሎ የውሸት መረጃ ኢሕአፓን፣ አመራሩንና አባላቱን በሚመለክት መልዕክት ለማስተላለፍ ጥሯል። ይህ ግለሰብ አንጃ ሆኖ ከሄደበት ከ2000 ዓም በኋላ ቢያንስ 2 የድርጅቱ ጉባኤዎች ተካሄደዋል። ክፍተኛ አመራር ኮሚቴ አባላት ተመርጠዋል።ይህ ሆኖ ባለበት ነው ድርጅቱን ሁለት ግለሰቦች ተቆጣጥረዋል፣ ከፍለዋል፣ አባላትን በትነዋል በማለት በጽሑፉ ገጽ 2 አንቀጽ 3 ላይ የሚያቀርበው። ራሱን አባል በነበረበት አንጃ ውስጥ የነበረውን ከሃዲ መርሻ ዮሴፍን ተክትሎ በመሄዱ ማውቀስ ሲገባው በብዙ አባላት ተመርጦ በከፍተኛ አመራር ኮሚቴ ውስጥ የሚገኘውን የድርጅቱን ነባር አባልን በማይመለከተው ገብቶ ለማክሰስ መጣር ሌላ ተልዕኮ ነው። በ1984ዓም አዲስ አበባ ገብተው የነበሩት ከሃዲዎች ልክ እንደዚሁ ግለሰብ ሲከሱት የነበረው የድርጅቱን አመራር ነበር። ዓላማቸው አመራሩን አጥቅተው ኣባላትን ተስፋ ለማስቆረጥና ለማከፋፈል ነው። የወያኔንና የተረኞችን ጠበብ ዘረኞች በድርጅቱ ላይ ጥቃት ለማድረስ የሚፈጽሙትን ደበ ከግብ ለማድረስ የታቀደ ነው።

አንጃዎች ከድርጅቱ ተለይተው የስርዓቶቹ መጠቀሚያ ሆነው መከሰታቸውንና የነበሩበት ድርጅትና አባላት አጥቂዎች መሆናቸውን ለመደበቅ ድርጅቱ ተከፈለ በማለት ሕዝብን ለማወናበድ ክፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛሉ። ይህ የተካኑበት ተግባር ነው። በኢትዮጵያ ታሪክ ጉባኤ ተካሄዶ ሀሳቡን ለውይይት አቅርቦ የተከፈለ ድርጅት የለም። በኢሕአፓ ውስጥ የተከሰቱት አንጃዎች በሙሉ ሀሳባቸውን በድርጅቱ ጉባኤ ላይ እንዲያቀርቡ ድርጅቱ ሁኔታዎችን እየመቻቸ በነበረበት ወቅት ነው ውስጥ ለውስጥ ተደራጅተው አለን ያሉትን ሀሳባቸውን ሳያቀርቡ የሸሹት። በእነሱ ዘንድ እውነት የለም ። ትናንትም ሆነ ዛሬ ውሸትና ክህደት እንጂ ። ሕዝብ እነዚህን የትግል ጸሮችን ለይቶ በማወቅ ከጥቅም ውጭ ማድረግ አለበት።

## ***<u>የታዋቂ ግለሰቦችን ስም መጠቀሚያ በማድረግ ውሸትን ማሰራጨት</u>***

ይህ ግለሰብ በጽሑፉ ገጽ 3 አንቀጽ 4 ላይ  ጳውሎስ ኞኞ የኢትዮጵያ መሪዎች የነበሩትን በሚመለከት የተጻፉትን መጻሕፍትንና የታሪክ ባለሙያዎችን በማናገር ለመጽሀፍ አብቅቶ አስነብቧል ይልና የኢሕአፓንም ታሪክ በድርጅርቱ ውስጥ ያልነበሩ ተፈላጊዉን መረጃ ካገኙ መጽሐፍ ይችላሉ በማለት ድርጅቱ በዚህ መልኩ የሚጻፉትን እንደሚቃወም አድርጎ ለማቅረብ ሞክሯል።ኢሕአፓ ለኢትዮጵያ ህዝብ የሚታገል ድርጅት ነው። እውነተኛ ታሪኩ እንዲጻፍ ይፈልጋል። የሚቃወመው በድርጅቱ ላይ የኢትዮጵያ ጠላቶች፣ አንጃዎችና አስመሳዮች የሚጽፉትን  ከሀቅ የራቁ መጻሕፍትንና ሌሎች ትረካዎችን ነው። እንዲሁም ጸሐፊ ነን ባዮችንም በማታውቁት ውስጥ አትግቡ ይላል።ይህን ማድረጉ ትክክል ነው። አለበለዚያ አያገባው ገብቶ ይፈተፍታል። ለምሳሌ ከላይ እንደተመለከተው በያ ትውልድ ተቋም በከምባታና ሀዲያ አውራጃ በቀይ ሽብር ሕይወታቸውን ያጡትን ታጋዮች በሚመለከት የተቀመጠው የውሸት መረጃ አንዱ ነው። ተቋሙ በድረገጹ ያስቀመጠውን የስም ዝርዝር ከአሲምባ ድረገጽ መውሰዱን ለመደበቅ ሲል በአካባቢው ያልነበሩና የቀይ ሽብር ሰለባም ያልሆኑ 8 ሰዎችን ከዝርዝሩ ውስጥ ከቷል። እንደዚህ ዓይነቱንና  ሌሎች የውሸት ጸሐፊዎች ነን ባዮችን ነው ድርጅቱ የሚቃወመው። ከታዋቂው ጳውሎስ ኞኞ ስራዎች ጋር የራሱን  ለማወዳደርም ሞክሯል።ይህማ ወርቅን ከድኝ ጋር እንደማወዳደር ይቆጠራል።ለአገራቸውና ለሕዝባቸው ስልጣኔና ብልጽግና ሲሉ የወደቁ ታጋዮች ታሪክ  በየቦታው በአግባቡ ተመዝግቦ የተቀመጠ መሆኑን ማወቁ አስፈላጊ ነው።የሚያውቋቸው ታጋዮችና አብረው ታስረው የነበሩ ዛሬም አሉ ። የዚህ ተቋም መስራችና የዚህ መጽሀፍ ደራሲ ነኝ በማለት የማስመሰል ሚና እየተጨወቱ በድርጅቱ ላይ መዝመት የጠላትነት ጥግ ነው።

ግለሰቡ በጽሑፉ ገጽ 9 በመጨረሻው አንቀጽ ላይ የድርጅቱን አባላት የውጪና የአገር ቤት በማለት ይከፋፍላል። አገር ቤት ቤት ያላችሁ ከድርጅቱ ተለይታችሁ  የአገር ቤቱን ኢሕአፓ( የኢሕአፓን ስም ሰርቆ አገር ቤት የገባውን አንጃ ማለቱ ነው) አጠናክረችሁ ለብቻችሁ ተደራጁ ይላል። አገር ቤት የገባው አንጃ በከሃዲው መርሻ ዮሴፍ ጋር አብሮ የሚሰራ መሆኑ እየታወቀ የተለያ አድርጎ በማቅረብና ከግለሰቡ ጋር የተለየ በማስመሰል የድርጅቱ አባላት በአንጃው ዙሪያ እንዲሰበሰቡና እንዲያጠናክሩ ይጠይቃል። አንዱን ሀቀኛ የከፍተኛ አመራር ኮሚቴ አባልን በግል ስም በመጥቀስ ከእውነተኛውና በሕቡዕ ከሚሰራው ኢሕአፓ ግንኙነት የቀድሞ አባላት እንዳያደርጉ ያሳስባል። ከዚህ የበለጠ ጠላትነት ምን አለ። ይህ አታላይ ግለሰብ የቆመበት መሰረት ግልጽ ነው። ድርጅቱ ተጠናክሮ እንዲወጣ አይፈልግም። አባላት ከድርጅቱ  ጋር ግንኙነት እንዳያደርጉ ጥረት ያደርጋል። አመራሩን ጥላሸት በመቀበት አባላት እንዲሸሹ ለማድረግ ምክር ይሰጣል። ይህ የማን ተልዕኮ ነው? ወያኔንና የተረኞችን ጠበቦች አገዛዝ ደግፎ ማቆም ነው። የዚህ ተቋም መስራች፣ የዚህ መጽሐፍ ደራሲና የኢሕአፓ ጉዳይ ይመለከተኛል ማለቱ ህዝብን ለማወናበድ የመጠቀሚያ ዘዴ ነው።

## ***ማጠቃለያ***

የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላቱንና ወዳጁን ለይቶ የሚያውቅ ሕዝብ ነው።አንድ መወገድ ያለበት ጉዳይ ግን አለ፣ነፍሰገዳዮች ፣ የስልጣን ጥመኞች፣ ዘራፊዎች፣ ሌቦችና  አስመሳዮች በየጊዜው ለማጭበርበር የሚሞክሩትና ጥቃትም እያደረሱ ያሉት ባንድ የአገዛዝ ስርዓት ላይ በተለያዩ የስልጣን እርካብ ላይ ሆነው በሕዝብም ሆነ በአገር ላይ ወንጀል የፈጸሙ ግለሰቦች አገዘዙ ሲወገድ ስላዳረሱት ወንጀል በይሉኝታ ተውጠን ስለማንጠይቃቸው እነዚህ የለመደባቸው ወንጀለኞች መልካቸውን ቀይረው ጥቃት እንዲያደርሱ ዝም መባሉ ነው።በተለያዩ ጊዜያት የዚህ ዓይነት ድርጊቶች እንዲፈጸሙ አመቺ ሁኔታዎች መፈጠሩ እንደተጠበቀ  ሆኖ  በአሁኑ ወቅት ለዚህ ዋና ምሳሌ የሚሆነው ትናንት ከወያኔ ጋር በመሆን ለ27 ዓመታት በሕዝብ ላይ ከፍተኛ በደል ሲፈጽሙ ከነበሩት ውስጥ ኮሎኔል አቢይ አህመድ “ስንኖር ኢትዮጵያዊ ስንሞትም ኢትዮጵያዊ እንሆናለን” ፤ አቶ ለማ መገርሳ “ ኢትዮጵያዊነት ሱስ ነው”  በማለት የሕዝብን ልብ ሊያማልል የሚችሉ ስንኞችን ተጠቅመው ሲቀርቡ የለውጥ ቡድን ናቸው፤ ኢትዮጵያዊ ሙሴ ነው፤ ነቢይ ነው፤ ከእግዚአብሔር የተላከ ነው፣  ብለን መቀበላችን ነው። ሹሙ ኮሎኔል በአሁኑ ወቅት ከኢትዮጵያ የውስጥ ጠላቶች ከእና ኦነግ ጋር በማበር ኢትዮጵያን የጽንፈኞች መፈንጫ በማድረግ አገሪቱን በመበጥበጥ ላይ ይገኛል። አቢይና ጽንፈኞች የአገሪቱን ሀብት  በመዝረፍ ዜጎችን በመግደል፣ ከኑሯቸው በማፈናቀል በማሰቃየት ላይ ናቸው ። የሹሙ አገዛዝ ባለሰልጣናት እውነቱን  ከሕዝብ ለመደበቅ ሸፍቶች በማለት የሚጠራው ቡድን ኮሎኔሉ ሰላይ በመሆን ሲያገለግለው የነበረውና አሁንም አብሮ የሚሰራው፣   20 ባንኮችን ዘርፈው፣ ትምሕርት ቤቶችን እንደ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ማዕከል በመጠቀም ሰራዊት አሰልጥነው፣ ዜጎችን በማሰቃየት ላይ የሚገኛው በምዕራብ ወለጋ የምንቀሳቀሰው የኦነግ  ሰራዊት በደምቢዶሎ ዩኒቨርስቲ  የአማራ ተወላጅ የሆኑ በአብዛኛው ሴቶች የሆኑ ተማሪዎችን ከ2 ወር በላይ አግቶ በመያዝ የሽብር ተግባር እንዲፈጸም አድርጓል።

እንዲሁም የዚህ የጠበብ ዘረኞች አገዛዝ ቁንጮ አገራችንን የውጭ ጠላቶች ሳውዲ አረቢያ፣ አረብ ኤሜሬትስ፣ ኳታር፣ ግብጽና የምዕራብ አገሮች መጫወቻ አድርጓል። የአገሪቱን ትላልቅ የኢኮኖሚ ተቋማትን አየር መንገድን ፣ ቴሌን፣ ባንክና መብራት ኃይልን በእንቤስትሜንት ስም ለመሸጥ በማስማመቱ በኖርዌይ የሰላም የኖቤል ተሸላሚ አድርገውታል። በሕዝብ ላይ የሚደርሰው ዘርፈ ብዙ በደል ማለትም ግድያ፣ ማፈናቀል፣ ሰውሮ ማጥፋት፣ ከስራ ማስወገድ፣ከትምሕርት ገበታ ተማሪዎችን ማስወገድና አግቶ መያዝ፣ የዜጎች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ረገጣ፣ የእምነት ተቋማት ቃጠሎና ዝርፊያ እንዲሁም የካህናትና ምዕመናን ግድያ በሰፊው በቀጠለበት በአሁኑ ወቅት ለአገራቸው ስልጣኔና እድገት፣ለሕዝባቸው የኑሮ ሁኔታ መሸሸል ሲሉ ሰማዕታት የሆኑ ታገዮች የሰጡትን የአደራ ቃል የራሱ፣ ድርጅቱ ያነሳቸው መሰረታዊ ጥያቄዎች እንዲመለሱ የማይፈልጉ አንጃዎችና አስመሳዮች ይህን ዘረኛ የአገርና የሕዝብ ጠላት የሆነውን አገዛዝ የሌላ ስም በመስጠት አገር ወዳድና የለውጥ ቡድን ነው በማለት የህዝቡን ትግል ለመጉዳት በመቅነዝነዝ ላይ ናቸው። የአሁኖቹ የኢሕአፓ ስም ሰራቂ አንጃዎችና አስመሳዮች እንደነ ነሲቡ ዓይነቶች ኢሕአፓ ሳይሆኑ በድርጅቱ ስም የሚነግዱ መሆናቸውን የቀድሞ አባላትና ሕዝብ ነቅቶ በመጠበቅ ለውሽታቸው ቦታ ሳይሰጥ ፣ የምርጫ ቧልታቸውንም ከግምት ውስጥ ሳያስገባ በጊዜያዊ የሽግግር መንግስት ምስረታ መንገድ ሕዝባዊና ዴሞክራሲያዊ ቋሚ መንግስት ለመምስረት ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ትግሉን መቀጠል አለበት ። እውነት ተደብቆ እንዳይቀር ኢሕአፓ የሀቀኞች ቤት መሆኑን በተለይ የቀድሞና የአሁኑ አባላት የድርጅቱን የትግል ታሪክ ለአዲሱ ትውልድና ለሌላውም ህዝብ በማስተማር ግዴታዎችን መወጣት ያስፈልጋል።

ድል የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው!!

እውነት ተደብቆ አይቀርም!!

የሽግግር መንግስት ይመስረት!!